# በንብረትዎ ላይ ዛፍ በመትከል ተመላሽ ማግኘት ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሀብት ይወቁ።

በዲሲ ውስጥ ያሉ ነዋሪዎች በመኖሪያ ወይም የንግድ ንብረቶች ላይ የጥላ ዛፎችን ሲተክሉ፣ ተመላሽ ሊያገኙ ይችላሉ። የጥላ ዛፎች በአፈር ውስጥ ያለውን የዝናብ ውሃ በማያዝ፣ ወደ ወንዞቻችን የሚገባውን የተበከለ ውሃ ይቀንሳሉ። እኛ—የዲሲ መንግስት— የአንድ ጊዜ ተመላሽ **በዛፍ ከ $50-100** እስከ ዛፍዎ ዋጋ ድረስ እናቀርባለን (ታክስና የመጓጓዣ ወጪን አይጨምርም)። የተመላሽ መጠንዎ የሚወሰነው በሚተክሉት የዛፍ አይነት ነው። **እስከ 25 ዛፎች በአንድ ንብረት ድረስ** የሚሆን ተመላሽ ሊቀበሉ ይችላሉ።

ይህ ፕሮግራም RiverSmart Rebates ሲባል የቀረበውም በኢነርጂ እና አካባቢ ዲፓርትመንት ከ Casey Trees ከሚባል ለትርፍ ከማይሰራ ድርጅት ጋር በመተባበር ነው።

## ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ።

በዲሲ ውስጥ የመኖሪያ ወይም የንግድ ህንጻ ካለዎት ወይም ከተከራዩ፣ ብቁ ነዎት። ቤትዎን ተከራይተውት ከሆነ፣ ተክሉን ለመትከል ከአከራይዎ ፈቃድ መጠየቅ ያስፈልግዎታል።

የሚያመለክቱበት ንብረት ዲሲ ውስጥ እስከሆነ ድረስ ለማመልከት ዲሲ ውስጥ መኖር አይጠበቅብዎትም።

## ያመልክቱ።

1. ቢያንስ 15 ጫማ ርዝመትና ስፋት ሊያድግ የሚችል ዛፍ ይግዙ።
2. ባለፉት ጊዜያት የከለከልናቸውን እነዚህን የዛፍ ዓይነቶች ያስወግዱ፤ ለእኛ ሥነ ምህዳር ጎጂ የሆኑ፣ በጣም ትናንሽ ወይም ለተባዮች የተጋለጡ ናቸው። ደረሰኝዎን ይያዙ።
3. የኦንላይን ማመልከቻ ያስገቡ እንዲሁም ደረሰኝዎን ያያይዙ።

ለዛፍዎ ደረሰኝ ከተቀበሉ በአንድ አመት ውስጥ ማመልከት ይችላሉ። በአመቱ ውስጥ ባለው በማንኛውም ጊዜ ለተመላሽ ማመልከት ይችላሉ ነገር ግን ዛፍ ለመትከል ምርጡ ጊዜያት ፀደይ እና መኸር መሆናቸውን ያስተውሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

### ካመለከትኩ በኋላ ምን ይሆናል?

1. ማመልከቻዎ ሙሉ ካልሆነ፣ Casey Trees ይደርሳሉ እንዲሁም አስፈላጊ የሆነውን ሰነድ ይጠይቃሉ

2. ገንዘብ ወዲያው የማይገኝ ከሆነ፣ Casey Trees ከ 2-6 ሳምንታት ውስጥ በማመልከቻዎ ባለው አድራሻ በኩል ለተመላሽዎ ቼክ ይልካል። በሚያመለክቱበት ጊዜ ገንዘብ ከሌለ፣ ገንዘብ በሚኖርበት ጊዜ ተመላሽዎን ያገኛሉ (ብዙ ጊዜ በየአመቱ ኖቬምበር ላይ)።
3. ዛፍዎን በመደበኛነት በተለይ ደግሞ በበጋ ወቅት ውሃ ያጠጣሉ እንዲሁም በአመት ሁለቴ ዛፍዎን ይከርክሙ። ዛፍዎ በሚያድግበት ጊዜ መከርከም ያስፈልገዋል። የዛፍ እንክብካቤ መመሪያን ይከተሉ።

ማመልከቻዎ ፈቃድ ካላገኘ፣ ባመለከቱ በሁለት ሳምንታት ውስጥ በኢሜይል እናሳውቅዎታለን።

**ሁሉም ብቁ አመልካቾች ተመላሹን ያገኛሉ?**
አዎ። የእኛን ዛፍ ለመምረጥና ለመትከል ያሉትን መመሪያዎች እስከተከተሉ ድረስ፣ በአንድ ንብረት እስከ 25 ዛፎች ለሆኑ ተመላሽ ያገኛሉ።

**ማወቅ ያለብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?**
እኛ—የዲሲ መንግስት— ለአንዳንድ የዛፍ አይነቶች ተመላሾችን አናቀርብም፡

- የተለያዩ crape myrtle፣ Japanese Maple እና አንዳንድ 'weeping' ዛፎችን አጠቃልሎ፣ 15 ጫማ ርዝመትና ስፋት ድረስ የማያድጉ ዛፎች
- ለእኛ ሥነ ምህዳር አካባቢያዊ ያልሆኑ እንዲሁም በአካባቢው ላይ ጉዳትን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ የሚታወቁ ዛፎች ወይም ወራሪ ዝርያዎች ተብለው የሚታወቁት
- the Emerald Ash Borer በሚባል እየተመገባቸው ባለ ጥንዚዛ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ በከፍተኛ ፍጥነት እየሞቱ ያሉ የ Ash ዘሮች

ባለፉ ጊዜያት ለእነዚህ ልዩ ዝርያዎች ተመላሾችን ከልክለናል።

**ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?**
መጀመሪያ፣ ከገጹ ታች በታ ላይ የሚገኘውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ይመልከቱ። አሁንም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን የእኛን አጋር Casey Trees በ (202) 833-4010 ላይ ያግኙ። ወይም በ treerebate@caseytrees.org ላይ በርዕሰ መስመር "Tree Rebate Question" ብለው ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

ስለ ፕሮግራሙ ዲሲ መንግስት ውስጥ ያለን አንድ ሰው ለማነጋገር ከፈለጉ፣ እባክዎ የእኛን RiverSmart Homes ቡድን በ (202) 535-2252 ላይ ከሰኞ እስከ አርብ፣ ከ 9 am እስከ 5 pm ድረስ ማነጋገር ይችላሉ። ወይም በርዕሰ መስመር "Tree Rebate Question" ብለው በ riversmarthomes@dc.gov ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

**በፍጆታዎቼ ላይ አሁንም እርዳታ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?**
ቤትዎን የበለጠ ለአካባቢ ተስማሚ የሚያደርጉ እርስዎን ሊረዱ የሚችሉ ሌሎች መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ።

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

### ተመላሼ የሚሰላው እንዴት ነው?

የተመላሽ መጠንዎ የሚወሰነው በሚተክሉት የዛፍ አይነት ነው። ትላልቅ ጥላ መፍጠር የሚችሉ እና የበለጠ የአካባቢ ጥቅማጥቅሞችን የሚያቀርቡ እንደ ኦክ እና ሂክሪ የመሳሰሉ የዛፍ ዝርያዎችን ከተከሉ፣ $100 ተመላሽ ያገኛሉ። ከስር ካሉት ልዩ ሁኔታዎች ዝርዝር ወጪ፣ ለሌሎቹ ብዙ ዝርያዎች $50 ተመላሽ ያገኛሉ።

### በመንገድ ላይ ለተተከለ ዛፍ ተመላሽ ማግኘት እችላለሁ?

አይ፣ በእግረኛ መተላለፊያና በመንገድ ላይ ያሉትን አጠቃልሎ፣ በህዝባዊ ስፍራዎች ለተተከሉ ዛፎች ተመላሾችን አናቀርብም። ነገር ግን፣ በ 311 ላይ በመደወል፣ ለእርስዎ ቅርብ የሆነ መንገድ ላይ ዛፍ ለመትከል መጠየቅ ይችላሉ።

### ዛፍ እንዴት እንደሚተከል አላውቅም። ምን ማድረግ አለብኝ?

ዛፍን በአግባቡ መትከል ቀላል ነው ነገር ግን መዘጋጀት ይኖርብዎታል። ያንን ማድረግ የእርስዎ ዛፍ መሬት ውስጥ ከተተከለ በኋላ እንደሚያድግ ማረጋገጫ ይሆናል። በ Casey Trees ድረ ገጽ ላይ ዛፍ እንዴት በትክክል መትከል እንደሚቻል የበለጠ ይወቁ።

### ዛፌን ለመትከል ወይም እንደ ዝናብ በርሜል ወይም የዝናብ አትክልት ስፍራ የመሰሉ ብቁ የአረንጓዴ ፕሮጀክቶችን ለመዘርጋት እርዳታ ማግኘት እችላለሁ?

ምን አልባት! የእኛ RiverSmart Homes ፕሮግራም ዝቅተኛ ዋጋዎች እና ለዝናብ በርሜሎች፣ ዛፎች፣ የዝናብ አትክልት ስፍራዎች እንዲሁም ቤይስኬፒንግ የማዘጋጀት እርዳታዎችን ያቀርባል። ነጠላ የቤተሰብ ቤት (ወይም አራት ወይም ከዛ በታች ክፍሎች ያሉት ህንጻ) ካለዎት፣ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በ RiverSmart Homes እርስዎ ዛፍ ለመትከል ምንም አይከፍሉም እንዲሁም ፕሮግራሙ 17 የዛፍ አማራጮችን ያቀርባል።

የ RiverSmart Rebates የመኖሪያ ህንጻ፣ የንግድ ህንጻ እንዲሁም የማህበረሰብ ቦታን ጨምሮ ለማንኛውም የንብረት ባለቤት ክፍት ነው። የሚከተለውን ከመረጡ፣ ከ RiverSmart Homes ይልቅ ይህ በተሻለ ተስማሚ ሊሆን ይችላል፡

- በ RiverSmart Homes ያልቀረበ የዛፍ ዝርያን ይምረጡ
- ዛፍዎን ለመትከል ረጃጅም የመጠበቅ ጊዜያትን ያስወግዱ

## እንደ ዝናብ በርሜል ወይም የዝናብ አትክልት ስፍራ ያሉ ሌላ አረንጓዴ ፕሮጀክቶችን ተመላሽ ማግኘት እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?

በራስዎ ወይም እርስዎ በመረጡት ገንቢ ባለሙያ የአረንጓዴ ፕሮጀክቶችን ሲገነቡ፣ ከእኛ - የዲሲ መንግስት ተመላሽ መቀበል ይችላሉ። የብቁነት መስፈርት፣ የማመልከቻ ሂደት፣ እንዲሁም የተመላሽ መጠን በፕሮጀክቱ አይነት ላይ በመመስረት ይለያያል እንዲሁም ከመገንባትዎ በፊት መተግበር ሊኖርብዎት ይችላል። ተመላሽ ስለምንሰጥባቸው የሚከተሉት ፕሮጀክቶች የበለጠ መማር ይችላሉ:

- በኋላ ላይ የአትክልት ቦታዎን ለማጠጣት ወይም መኪናዎን ለማጠብ የሚሆን የዝናብ ውሃ የሚያጠራቅምና የሚይዙ **የዝናብ በርሜሎች**
- **የዝናብ ውሃን ለመያዝ የሚያስችሉ ተክሎችን እድገት ለመርዳት የሚሆኑ** አረንጓዴ ጣሪያዎች
- ከተለመደው አስፋልትና የኮንክሪት ገጽ ይልቅ የዝናብ ውሃን ለመያዝና በጊዜያዊነት ለማቆየት የሚያስችሉ **አስተላላፊ ገጽታዎች**
- **የዝናብ አትክልት ስፍራዎች** ወይም ከዝናብ ውሃ ውስጥ ያለውን ብክለት ለማጣራት፣ ኢንጂነሪድ የሆነ ሌላ የአትክልት ስፍራ ሲስተም

## ዛፍ ለመትከል ሌላ ማንኛውም የገንዘብ እርዳታ ማግኘት እችላለሁ?

አዎ! ለዚህ ፕሮግራም ሲያመለክቱ፣ በ DC Water ክፍያዎ ላይ RiverSmart Rewards ለሚባለው ቅናሽ ማመልከት እንዲችሉ እንረዳዎታለን። እንደ ጥላ ዛፎች የመሰሉ አረንጓዴ ፕሮጀክቶች ጋር ያሉ ንብረቶቻቸውን ከዝናብ ውሃ ለሚከላከሉ የንብረት ባለቤቶች የተደረገ ቅናሽ ነው።

## እነዚህ አረንጓዴ ፕሮጀክቶች የዲሲ ከተማን እንዴት ሊረዱት ይችላሉ?

እንደ የዝናብ በርሜሎች፣ የዝናብ አትክልት ስፍራዎች እንዲሁም የጥላ ዛፎችን የመሳሰሉ አረንጓዴ ፕሮጀክቶች ንብረትዎን የሚያጥለቀልቀውን እና ወደ ወንዞች የሚፈስሰውን የተበከለ የዝናብ ውሃ መጠን እንዲቀንስ ይረዳሉ። ይህ የ Anacostia ወንዝን፣ Potomac ወንዝን እንዲሁም Rock Creek ከአደገኛ ብክለቶች እንድንጠብቅ ይረዳናል።

## ተቀባይነት ሳላገኝ ብቀር ለፕሮግራሙ እንደገና ማመልከት እችላለሁ?

አዎ። በሁኔታዎ ላይ ያለው ለውጥ ብቁ ያደርገኛል ብለው ካመኑ፣ እንደገና ለተመላሽ ማመልከት ይችላሉ።

ተቀባይነት አግኝተው ነገር ግን ባመለከቱበት ወቅት ገንዘብ ከሌለ፣ ዳግም ማመልከት አያስፈልግዎትም። ገንዘብ ሲገኝ (ብዙውን ጊዜ በየአመቱ ኖቬምበር ላይ ነው) የእርስዎን ተመላሽ በፖስታ እንልክልዎታለን።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ሜይ 2021 ነው።*